የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

ከህዳር 11-ህዳር 17 ፣2017ዓ.ም
(November 20-26/2024)
Week Three

## 1.ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመርያ ከወለድ ነፃ ባንኮችን አላማከለም ተብሎ ቅሬታ ቀረበበት

**ሪፖርተር፡November 24, 2024**

በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች እርስ በርስ እንዲበዳደሩ የሚያስችል መመርያ ቢያወጣም፣ መመርያው ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮችን ያማከለ አይደለም ተብሎ ቅሬታ ቀረበበት፡፡
የዘምዘም ባንክ ስትራቴጂ ኦፊሰር ኃላፊ አቶ እንድሪስ ዑመር ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ከሌሎች ባንኮች ለመበደር ቢፈልጉ ብሔራዊ ባንክ የዘረጋው ሥርዓት አይፈቅድም፡፡
ብሔራዊ ባንክ ያወጣው ባለሁለት ገጽ መመርያ የብድሩን ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም የመመለሻ ቀናትን፣ የወለድ መጠንን፣ ለተበዳሪ የሚያስፈልጉ መሥፈርቶችንና ሌሎች ጉዳዮችን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ከወለድ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች እንዴት እንደሚሳተፉ እንደማይገልጽ አስረድተዋል፡፡
ከወለድ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች የገንዘብ እጥረት ገጥሟቸው ከሌሎች ባንኮች ለመበደር ቢፈልጉ፣ በወለድ እንጂ ከወለድ ነፃ መበደር እንደማይችሉ መመርያው እንደሚደነግግ አክለው ገልጸዋል፡፡
በተመሳሳይ ይህንኑ አገልግሎት ለማግኘት ብሔራዊ ባንክ ዘንድ ቢሄዱም፣ ብሔራዊ ባንክ 18 በመቶ ወለድ ከፍለው መበደር እንዲችሉ የሚፈቅድ ሕግ እንጂ የተለየ አሠራር እንደሌለው አስታውሰዋል፡፡
በተለይ በኢኮኖሚው ውስጥ የቢዝነስ ፖሊሲው ከወለድና ከወለድ ነፃ ባንኮችን ያካተተ ሥርዓት መሆን ሲኖርበት፣ አሁን እየወጡ ያሉ መመርያዎች ከወለድ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ችላ የሚሉና በወለድ የሚሠሩትን ባንኮች ደግሞ የሚደግፉ ናቸው ብለዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135732/

## 2. አምራቾች በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ላይ ያቀረቧቸው ጥያቀዎችና የመንግሥት ምላሽ

**ሪፖርተር፡ November 24, 2024**

መንግሥት ተግባራዊ ማድረግ በጀመረው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የተገኙ ውጤቶችንና ምጣኔ ሀብታዊ ሽግግርን በተመለከተ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ትልቅ የምክክር መድረክ አዘጋጅቶ ከልማት አጋሮች፣ ከአምራች ኢንዱስትሪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ሲያካሂድ ሰንብቷል።
በምክክር መድረኩ ኢትዮጵያ እየተገበረቻቸው ያሉ ፖሊሲዎችና የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) ዘለግ ያለ የመወያያ ጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን፣ በገለጻቸውም ‹‹ከአገራዊ ለውጡ›› በኋላ መንግሥት በተለይም ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዕውን መሆን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ፣ መንግሥት እየተገበረ ያለው አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያና የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትግበራ ለአገሪቱ ዕድገትና ዘላቂ ልማት መሳካት የላቀ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡
ፍፁም (ዶ/ር) አኃዛዊ መረጃዎችን በማቅረብ ከገለጿቸው ጉዳዮች ውስጥ መንግሥት የኢትዮጵያን የውጭ የዕዳ ጫና ለመቀነስ ባለፉት ስድስት ዓመታት የአሥር ቢሊዮን ዶላር ዕዳ ክፍያ መፈጸሙንና በተጠቀሱት ስድስት ዓመታት ውስጥ የዕዳ ክፍያ ከመፈጸም ባለፈ ከውጭ ምንም ዓይነት የንግድ ብድር እንዳልወሰደ መናገራቸው ይጠቀሳል፡፡
የፕላንና ልማት ሚኒስትሯን ማብራሪያ ተከትሎ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው አኳያ በተለይም ወቅታዊውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርምን ጨምሮ አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ያመጣውን ዕድልና የዘርፉን ፈተና የተመለከቱ ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት ተደርጓል፡፡
በውይይቱ ተሳታፊ ከነበሩት መካከል የኢትዮጵያ ሥጋ አምራችና ላኪዎች ማኅበር የቦርድ ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ከሊፋ ሁሴን፣ በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የሥጋ አምራች ዘርፍ ችግሮችን የቀለለር

## 3.የቻይና ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው- ያንግ ይሃንግ (ዶ/ር)

**ኢዜአ፡ ህዳር 16/2017**

የቻይና ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር የኢኮኖሚ እና ንግድ ጉዳዮች አማካሪ ያንግ ይሃንግ (ዶ/ር) ገለጹ።
የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ ፍሰሃ ይታገሱ(ዶ/ር) ከአምባሳደሩ የኢኮኖሚ እና ንግድ ጉዳዮች አማካሪ ጋር ተወያይተዋል።
ውይይቱ የቻይና ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በኢንዱስትሪ ፓርኮችና በድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጠና እንዲጨምር ማድረግ ላይ ያተኮረ መሆኑን የኮርፖሬሽኑ መረጃ ያመለክታል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5513746

## 4. መንግስት ስታርታፖችን ለማጠናከር በሚያደርገው ርብርብ የበኩላችንን ድርሻ እንወጣለን

**ኢዜአ፡ ህዳር 16/2017**

መንግስት ስታርታፖችን ለማጠናከር በሚያደርገው ርብርብ የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ የተለያዩ ባለሀብቶች ተናገሩ፡፡
መንግስት በመላው ሀገሪቱ የሚገኙና በተለያዩ ዘርፎች ለመስማራት ውጥን የያዙ ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎችን በመደገፍ ወደ ስራ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል፡፡
የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ከኦርቢት ሔልዝ ጋር በመተባበር ስታርታፖችን ማጠናከርና መደገፍ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የምክክር መድረክ አካሒዷል፡፡
በመድረኩ ነባር ስራ ፈጣሪዎች ለአዳዲስ ስራ ፈጣሪዎች የህይወት ልምዶቻቸውን አካፍለዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5515152

## 5. ታሪካዊውን ግንኙነት በኢኮኖሚ ትብብር የማጠናከር ጥረት

በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ጫና አሳድረው የነበሩ ችግሮች ደረጃ በደረጃ መፍትሄ እያገኙ በመምጣታቸው በዘርፉ መነቃቃት እየታየ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃዎች ያመለክታሉ:: በ2016 የበጀት ዓመት በብዙ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የታየውን ተስፋ ሰጭ ውጤት ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል:: ለዚህ ውጤት መመዝገብ ሚና ከነበራቸው ግብዓቶች መካከል ኮሚሽኑ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን (Foreign Direct Investment – FDI) ለማሳደግ ያከናወናቸው ተግባራት ይጠቀሳሉ:: በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ሀገራትና በአዲስ አበባ የተካሄዱና ኮሚሽኑ የተሳተፈባቸው የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎረሞች (Business and Investment Forums) ደግሞ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው::Ethiopian press: November 21, 2024

የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎረሞች የኢንቨስትመንት አቅሞችንና እድሎችን በማስተዋወቅ ባለሀብቶችን ለመሳብ ትልቅ ሚና አላቸው:: በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አማራጮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ በሕግ ስልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ባለፈው የበጀት ዓመት በ10 ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረሞችና ኤግዚቢሽኖች ላይ ተሳትፏል::

https://press.et/?p=141233

## 6. Safaricom Ethiopia lobbies lawmakers for equal market access

**Reporter: November 23, 2024**

**"Safaricom pays taxes using Telebirr": External Affairs Chief**

The executives of Safaricom Telecommunications Ethiopia Plc have called for government support in ensuring equal access to open platforms, criticizing incongruent tariffs on phone services provided by competitor Ethio telecom.

During a visit to Safaricom headquarters this week, members of the parliamentary committee for Democracy Affairs heard CEO Wim Vanhelleputte, CEO of Safaricom Ethiopia, advocate for equal access to telecommunications networks, urging that all customers should be able to utilize both Safaricom and Ethio telecom networks without exclusion.

Safaricom's recently appointed Chief External Affairs Officer, Andualem Admassie (PhD), noted issues with off-net and on-net parity with Ethio telecom.

The state-owned operator's customers are charged extra when making phone calls to a number in the Safaricom network, while Safaricom has a fixed charge regardless of network.

https://www.thereporterethiopia.com/42698/

## 7. NBE warns financial institutions against illicit forex activities

**Reporter: November 25, 2024**

The National Bank of Ethiopia (NBE), the regulatory authority for the financial industry, has issued a warning to financial institutions and businesses involved in illicit activities related to the foreign exchange market. NBE supervisors have conducted on-site investigations into the foreign currency operations and management of every bank.

Recent macroeconomic reforms have enabled the country to increase its foreign exchange reserves over the last quarter of the year, facilitating the repatriation of profits by international corporations and airlines.

Significant changes were implemented as part of the macroeconomic reform initiated on July 29. These changes included the establishment of a free foreign exchange market and modifications to how the banking sector manages foreign exchange. Notably, citizens are now allowed to open foreign exchange accounts, and new forex bureaus have been established.

NBE Governor Mamo Esmelealem Mihretu reported that the reform has yielded positive and encouraging outcomes in its initial quarter. In an interview with Fana TV, he highlighted several new statistics and developments since the reform's inception.

For the first time in the nation's history, the balance of payments recorded a surplus. "The balance of payments showed a USD 573 million surplus, compared to a USD 1.2 billion deficit the previous year," he stated.

https://capitalethiopia.com/2024/11/25/nbe-warns-financial-institutions-against-illicit-forex-activities/

## 8. Ethiopia Advancing Endeavors towards Implementation of AfCFTA, Says State Minister

**ENA: November 24/2024**

Ethiopia is scaling up efforts for the successful implementation of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) agreement, State Minister of Trade and Regional Integration, Yasmin Wohabrebbi stated.

Ratifying the AfCFTA in 2019 and as part of Ethiopia's effort in domesticating the Agreement, the country has been developing its national AfCFTA implementation strategy.

This strategy comprises key sectors where the East African nation can gain a competitive advantage under the AfCFTA and integrate its economy into regional and global value chains.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5511144

## 9. Microeconomic Reform Revitalizes Private Sector Growth, Says ECCSA President

**ENA: November 23/2024**

Stabilizing the macroeconomy is among the economic policy measures taken to ensure the structural economic transformation in recent years.

The Ministry of Planning and Development convened a high-level sessions among various stakeholders including ambassadors, heads of UN agencies, development partners and representatives of international organizations to discuss Ethiopia's Economic Transformation driven by the implementation of the Homegrown Economic Reform. Numerous achievements have been acknowledged despite some challenges.

Accordingly, the implementation of the Homegrown Economic Reform has registered tangible results across the nation, it was learnt.

Among the outcomes of the macroeconomic reform is enhanced participation and benefits of the private sector, which are instrumental in achieving sustainable economic growth.

President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectorial Association Sebsib Abafira

in an exclusive interview with ENA, expressed that the macroeconomic reform has fulfilled a long-standing aspiration of the private sector.

Highlighting the indispensable role of the private sector for the overall development of the country, the president stated that the reform presents an opportunity to rectify longstanding issues.

In this regard, the regulation passed to privatize stated-owned economic sectors fully or partially will enable to build inclusive, competitive, and sustainable economic system, the president noted.

The manufacturing industry has been collaborating with the government to substitute imported products with locally produced items; imported products require high foreign exchanges, he elaborated, adding that the macroeconomic reforms have alleviated the previous foreign exchange bottlenecks facing the private sector in importing products and inputs.

He also noted that the macroeconomic reform is addressing operational inefficiencies within the business system.

Emphasizing the need for cooperation from all stakeholders in implementing macroeconomic reforms, the president assured that the private sector will exhibit continued cooperation and national responsibilities.

He highlighted Ethiopia's efforts to participate in various continental and global business environments, including the accession to the World Trade Organization, which requires strong competition and a robust private sector.

Finally, the president called on stakeholders, including financial institutions, to work together to strengthen the private sector.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5508221